# የሀገራችን ፖለቲካ ትልቁ በሽታ "የሸዋ ፖለቲካ" ነው

ለዚች ማስታወሻዬ የሰጠሁት ርእስ ከባድ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ አነታራኪም ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡ ግን ምንም መደባበቅ የለብንም - የሀገራችን ፖለቲካ ትልቁ በሽታ "የሸዋ ፖለቲካ" ነው፡፡ እኔ "የሸዋ ፖለቲካ" የምለው ሸዋን ማእከል አድርጎ ለዘመናት ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር የነበረውን የፖለቲካ ስርዓት ነው፡፡ ይህንን ኢህአዴግ "የነፍጠኛ ስርዓት" ይለዋል፡፡ ነፍጠኛነትንም ጥቅልል አድርጎ ለአማራው ብሔር ብቻ ይሰጣል፡፡ በዚህ አልስማማም፡፡

"የሸዋ ፖለቲካ" የሚለው ሐረግ አንዳንዶችን የሚያስከፋ ከሆነ "የመሐል አገር ፖለቲካ" በሚለው መተካት ይቻላል፡፡ "የሸዋ ፖለቲካ" በአንድ ብሔር ላይ የተንጠለጠለ አደለም፡፡ በቀድሞው የሸዋ ክፍለ ሀገር በርከታ ብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሉበት ነበር፡፡ በርካታዎቹ በሰሜንና በማዕከላዊው የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከሞላ ጎደል በሸዋ ፖለቲካ ውስጥ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ ያም ሆኖ፤ የጎላ ተሳትፎ የነበራቸው እነማን እንደነበሩም በግልጽ ይታወቃል፡፡

"የሸዋ ፖለቲካ" ዋነኛ መገለጫው "ሴራ፣ ሸርና ተንኮል" (በአጭሩ Conspiracy) ነው፡፡ ይህ ሴራ ከቤተ መንግስቱ (Palace Conspiracy) ጀምሮ በተዋረድ ይሄዳል፡፡ ሁለተኛው "የሸዋ ፖለቲካ" መገለጫ አሉባልታ ነው፡፡ አሉባልታውም የሚጀምረው ከዚያው ከቤተ መንግስት ነው፡፡ እሱም በተዋረድ ይወርዳል፡፡

ለዘመናት የዘለቀው የሴራና የአሉባልታ ፖለቲካችን እነሆ ዛሬም በዚያው ቅኝት እየተቀነቀነ ነው፡፡ አልቆመም፡፡ የሀገሪቱን የፖለቲካ ምህዳር ከጫፍ እስከ ጫፍ ወጥሮ ይዞ የሚንጣት ይኸው የገነገነ የሴራና የአሉባልታ ፖለቲካችን ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ለምሣሌ፡- በተቀዋሚው ጎራ ቅንጅትን የበተነው የውስጥ ሴራና አሉባልታ ነው፡፡ አሁን ያሉትን ፓርቲዎች ብል እንደበላው ጨርቅ የሚበጣጥሳቸው በውስጣቸው ያለው የሴራና የአሉባልታ ቫይረስ ነው፡፡

በኢህአዴግም መንደር ቢሆን ሴራውና አሉባልታው አለ፡፡ እዚያ አካባቢ ያለውን ሁኔታ ለየት የሚያደርገው ጠመንጃም እስር ቤትም መኖሩ ነው፡፡ ጠመንጃውና እስር ቤቱ፤ በኢህአዴግ ቤት ያለውን አሉባልታና ሴራ ውስጥ ውስጡን እንዲብላላ እንጂ አደባባይ እንዲወጣ አላደረገውም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሲብስበት (Climax ላይ ሲደርስ) ግን የኢህአዴግ ጎምቱዎች ጭምር ወደ ከርቸሌ ሲወርዱ ታይቷል፡፡

እናም፤ እንደ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ፣ ሴራና አሉባልታ በሽታችን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህንን በሽታ ይዘን ጤናማ ፖለቲካ ሊኖረን አይችልም፡፡ ጤናማ ፖለቲካ ከሌለን ደግሞ ጤናማ ኢኮኖሚና ጤናማ ማህበራዊ ግንኙነት ሊኖረኝ አይችልም፡፡ ይህንን ስር የሰደደና የገነገነ የመሐል አገር (የሸዋ ፖለቲካ) ይዘን ሀገሪቱንም ፖለቲካችንንም ወደተሻለ ደረጃ ማሸጋገር አንችልም፡፡

ይህንን በሽታ ከነሰንኮፉ ለመንቀል ደግሞ በቅድሚያ በሽታው ያለብን መሆኑን አምነን መቀበል ይጠበቅብናል፡፡ ይህንን ካደረግን በሽታው ግማሽ በግማሽ ፈውስ አገኘ ማለት ነው፡፡ በሽታውን ከደበቅነው እድሜ ልካችንን ስንገዘገዝ መኖር ነው፡፡ እድሜ ልካችንን እዬዬ እያልን መባጀት ነው፡፡ ዛሬ ባነን ይህንን የሀገርና የሕዝብ ፀር የሆነ በሽታ በድፍረት ካላወራንለት እኛን ከመብላት አልፎ ወደ ቀጣዩ ትውልድ መተላለፉ አይቀሬ ነው፡፡

የእኛ ዘመን ፖለቲካ ለይቶለት ተሰነካክሏል፡፡ እኔን የሚያሳስበኝ  የመጪው ዘመን፣ የመጪው ትውልድ ፖለቲካ ነው፡፡ የልጆቼና የልጅ ልጆቼ መጻዒ ዕድል ያሳስበኛል፡፡ እኔ የምመኘው መስዋእትነት የሚከፍል ሳይሆን፣ አሁን በምንከፍለው መስዋእትነት ተረጋግቶ የሚኖር ትውልድ ነው፡፡

እኔ በድፍረት ወጥቼ ይህንን ብያለሁ፡፡ ችግሩ የጋራ ስለሆነ እንወያይበት፡፡ ካለበለዚያ በቀጣይ ዓመታትም ፓርቲዎች ተተረተሩ፣ ተከፋፈሉ፣ ተበተኑ፣… የሚለው ዜና ቋሚና ዘላቂ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

(አብዱራህማን አህመዲን ዘእምነገደ ቁረይሽ፡፡ ሚያዝያ 1 ቀን 2007 እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር)

ahayder2000@gmail.com